# አራት ኪሎ ያሉ ባለሥልጣናት ያለባቸዉ ችግር !

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

ታህሳስ 13 ቀን 2002

ከሁለት ቀናት በኋላ የፈረንጆች፣ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ደግሞ የኢትዮጵያዉያን የገና በዓል ይከበራል። የገና በዓል ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰዉ ልጆችን ሁሉ ለማዳን ከእመቤታችን ድንግል ማሪያም በበረት ዉስጥ የተወለደበትን የምናስብበት ታላቅ ቀን።

ያለፈዉ አመት፣ በዚህ በገና በዓል ወቅት ነበር፣ አሥር የሚሆኑ የኢሕአዴግ የደህንነት አባላት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምን በሰደፍ ፊኛቸዉ ላያ የመቷቸዉና ተወዳጇ እህታችንን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በግፍና በጭካኔ እያዋከቡ ወደ ቃሊቲ  እሥር ቤት የወሰዷት።

በዚህ አመት ደግሞ አሁንም በገና በዓል ወቅት ጥቁር ካባ የለበሱ ዳኛ ተብዬ የአገዛዙ ካድሬዎች የደርግ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ሲያደርግ እንደነበረዉ፣ የሰዉ ነፍስ ባላጠፉ ዜጎች ላይ የሞት ፍርድ ሲበይኑ እያየን ነዉ።

አመት አልሆነዉም፣ የወያኔ/ኢሕአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሆኑት አቶ አባይ ጸሃዬ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ቃለ መጠይቅ አድርገዉ ነበር። በዚያ ቃለ መጠይቅ አንድ መሪ ሊኖረዉ ስለሚገባ ብቃት ሲናገሩ «አንድ መሪ በራሱ የሚተማመን መሆን አለበት» ነበር ያሉት። በራሱ የማይተማመን ሰዉ እራሱን መምራት አይችልም። እራሱን መምራት ያልቻለ ደግሞ ሌሎችን ሊመራ እንደማይችል ነበር እኝሁ የኢሕአዴግ ባለሥልጣን ያስረዱት።

አሁን በአራት ኪሎ በሥልጣን ላይ ያሉ ባለሥልጣኖች ምናልባትም አቶ አባይ ጸሃዬን ጨምሮ በራሳቸዉ የመተማምን ትልቅ ችግር ያለባቸዉ ይመስላል። በጣም በፍርሃትና በሥጋት ዉስጥ እንዳሉ ነዉ ድርጊቶቻቸዉ የሚያሳዩት።

ከሁለት ሺህ አመታት በፊት ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ከሩቅ አገራት ስብዓ ሰገል ወይንም ነገስታት፣ ሊሰግዱለት ከርቤ፣ ወርቅና እጣን ይዘዉ መጡ። «የተወለደዉ የአይሁድ ንጉስ ወዴት ነዉ ? » እያሉ ጠይቁ። «ንጉስ» በሚሉበት ጊዜ ምድራዊዉን ንግስና ማለታቸዉ አልነበረም፣ ከዚህ አለም ያልሆነ ሰማያዊና ዘላለማዊ ንግስናን እንጂ።

መጀመሪያ የሄዱት ወደ እየሩሳሌም የይሁዳ ዋና ከተማ ነበር። በዚያም ይገዛ የነበረዉን

ንጉስ ሄሮድስን አገኙት። ሄሮድስ «ንጉሥ» እንደተወለደ በሰማ ጊዜ ደነገጠ። ይህ የተወለደዉ ሕጻን ሥልጣኔን ሊወስድብኝ ነው ብሎ ፈራ። «በአንድ አገር ሁለት ንጉስ ሊኖር አይችልም። እኔ እያለሁ ሌላ ንጉስ አይኖርም» በሚል ውስጡ በምሬት ተሞላ።

በዚህም ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመግደል ተነሳ። ማን እንደሆነ በርግጠኝነት ማወቅ ሊቸግር ስለሚችል ከሁለት አመት በታች ያሉ የቤተልሄም ሕጻናት በሙሉ እንዲገደሉ ወሰነ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ማሪያምና ቅዱስ ዮሴፍ ግን አስቀድመዉ ወደ ግብጽ ሸሽተዉ ስለነበረ የሄሮድስ ሰይፍ ሳያገኛቸዉ ቀረ።

ሄሮድስ፣ እርሱ በሥልጣን እንዲቆይ ለማመቻቸት ሲል ብቻ፣ ስለፈራ፣ በራሱ ስለማይተማማን፣ መሰሪና ክፉ ስለነበረ ሕጻናትን አስጨረሰ። የንጹሃንን ደም አፈሰሰ። በበቀል መንፈስ ተንቀሳቀሰ።

አሁን በአገራችን ተመሳሳይ ሁኔታ ያለ ይመስላል። አራት ኪሎ ካሉ ባለሥልጣናት የምናየዉ የሄሪድስ አይነት የበቀልና የጭካኔ እርምጃ ነዉ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ምንም ያደረገቻቸዉ ነገር የለም። የሰበከችዉ ፍቅርን፣ ሰላምን ፍትህን ነዉ። እንደዉም ሌሎች «ወያኔዎች መወገድ ያለባቸዉ ጠላት ናቸዉ» ሲሉ ብርቱካን ሚደቅሳ ግን «ወያኔዎች ጠላት አይደሉም። ማንም ኢትዮጵያዊ የማንም ኢትዮጵያዊ ጠላት አይደለም» ብላ በድፍረት የተናገረችና ያስተማራች ታላቅ ሴት ናት።

ነገር ግን ወያኔ/ኢሕአዴጎች ለስድስት ወራት በጨለማ ቤት ዉስጥ አስቀመጧት። እስከ አሁን ድረስ ሊፈቷት ፍቃደኛ አልሆኑም። በቅርቡ አቶ መለስ ዜናዊ ለጋዜጠኖች በሰጡት ቃለ መጠይቅ ብርቱካን ከቃሊቲ እንደማትወጣ በድፍረትና በንቀት ነበር ሲናገሩ የተሰሙት።

**«ምንድን ነዉ ችግራቸዉ ?» ብለን ብንጠይቅ መልሱ ከባድ አይሆንም። ችግራቸዉ በራስ የመተማመን ችግር ነዉ። ዉስጣቸዉ ይፈራል። በዉስጣቸዉ ድንጋጤ አለ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በቅንጅት ጊዜ ከነበረዉ በባሳ መልኩ ሕዝቡን ታንቀሳቅስብናለች የሚል ፍራቻ አለባቸዉ።**

በተለይም እነ አቶ መለስ ዜናዊ በሥልጣናቸዉ እንዲቆዩ ይረዳቸዉ ዘንድ፣ የዘረጉት ስታሊናዊ የዘር መከፋፈል እንዲበጣጠስና በዘር ተከፋፍለዉ የነበሩ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያዊነት ድንኳን ዉስጥ እንዲሰባሰቡ፣ እነ አቶ ስዬ አብርሃና ዶር ነጋሶ ጊዳዳ የአንድነት ፓርቲን እንዲቀላቀሉ፣ መድረክ የተሰኘዉ አካል እንዲመሰረትና ትልቅ አገር አቀፍ አማራጭ እንዲሆን፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከጅምሩ ቁልፍ ሚና የተጫወተች ታላቅና አስተዋይ መሪ እንደሆነች ስለሚያወቁ ትልቅ ስጋት ዉስጥ ነዉ የከተተቻቸዉ። የርሷ ነገር ራስ ምታት ነዉ የሆነባቸው።

ለዚህም ነዉ ሊፈቷት ፈቃደኛ ያልሆኑት። የሄሮድስ መንፈስ ስለተቆጣጠራቸዉ፣ በራሳቸዉ ስለማይተማመኑ ሁኔታዎችን ትንሽ ለቀቅ ካደረጉ ሰዉ ሁሉ የሚነሳባቸዉ ፣ በሩን ከከፈቱ የሚዋጡ ይመስላቸዋል። ይህ ነዉ አራት ኪሎ ያሉ ባለሥልጣናት ችግራቸዉ !!!!

ልሳሳት እችላለሁ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም ላይ የእድሜ ልክ እሥራት እንጂ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸዉ አይመስለኝም። አሁን ግን የግንቦት ሰባት መሪዎችና የግንቦት ሰባት ደጋፊዎች ናቹህ የተባሉ ኢትዮጵያዉያን፣ የሞት ፍርድ ተበይኖባቸዋል። ይህ ዉሳኔ ምንም ትርጉም የማይሰጥ ዉሳኔ ነዉ። በምንም የሕግ መስፈርት ሚዛናዊና ፍትሃዊ ዉሳኔ ተደርጎ ሊወሰድ አይችለም። ኢትዮጵያ ዉስጥ የሕግ ሥርዓቱ መቀለጃ መሆኑን በገሃድ የሚይሳይ ነዉ።

ገዢዉ ፓርቲ ይህን አይነት እርምጃ አሁን የወሰደዉ በርግጥ እነዚህ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸዉ የተባሉ ኢትዮጵያዉያን ጥፋት አጥፍተዉ ሳይሆን በዚህ ሂደት ለዲሞክራሲና ለፍትህ የሚታገሉ ኢትዮጵያዉያንን ለማስፈራርት ነዉ። ይህ በራስ ካለመተማማንና ከፍርሃት የመነጨ የአገዛዙ ደካማና ርክሽ ስትራቴጂን ሚያሳይ ነዉ። እንዲህ አይነቱ ስትራቴጂ ለደርግም አልበጀም። ወደፊትም ለወያኔ/ኢሕአዴግ አይበጀዉም።

የተከበሩ ዳኛ መሸሻ ወልደሚካዔል «እረ እየተስተዋለ» በሚል ጽሁፋቸዉ ካቀረቡት፣ አቶ ስዬ አብርሃ ወደ እሥር ቤት መውረዳቸዉ በፊት በፍርድ ቤት የተነጋሩትን በመጠኑ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ፡

«እኔ የፈጸምኩት አንድም ኮራፕሽን የለም። ማስረጃም ጠላቶች አያገኙብኝም። እኔ ከመላ ቤተሰቤ ለእሥር የተዳረጉት **ወደ ስህተት ጎዳና ገብተናል። ሕዝቡ ጠልቶናል። ራሳችንንም ለምን አንፈትሽም ?”** እያልሁ የሕዝቡን ስሜት ከቀሪ ደኞቼ ጋር ካየሁና ካስተዋልሁ በኋላ ከመለስ ጋር መጨቃጨቅ ጀመርሁ። በተለይም በተፈጠረዉ የጦርነት ድል አጋጣሚ **በስህተት ያስወሰድነዉን ወደባችንን** ሳናስመለስ ጦርነቱን ማቆም የለብንም ብዬ በጣሙን ተከራከርኩ። ግን ባለዉ የጠቅላይ ጦር አዛዥነቱ ጦርነቱ እንዲቆም አደረገ። ከዚያም አልጀርስ ሮጦ በመሄድ ያንን እንደገና እጅ የሚያሰጥ ፊርማ አኑሮ መጣ። ከዚህ በኋላ በመካከላችን የነበረዉ ያለ መግባባት ፍጹም ሊጣጣም አልቻለም። **“ስህተታችንን ማረም አለብን”** ማለቴን አጠናከርሁ። ይህ የማርክሲዝም ሌኒንዝም አካሄድ አያዋጣንም። አመራራችንን በሊበራል ዲሞክራሲ መሰረት ላይ መሆን አለበት ብዬ ከጓደኞቼ ጋር መከራከሬን ቀጠልሁ። እናም መለስ እኔን ለማስወገድ በጠነሰሰዉ ተንኮል እስከነ ቤተሰቤ ለእሥር አበቃኝ። እዉነታዉ ይህ ስለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያወቅልኝ » ነበር አቶ ስዬ አብርሃ በፍርድ ቤት የተናገሩት።

አቶ ስዬ ከተናገሩት ዉስጥ «ሕዝቡ ጠልቶናል፣ እራሳችንን እንፈትሽ፣ በስህተት

ያስወገድነዉን ወደባችንን እንመለስ፣ ስህተታችንን ማረም አለብን፣» የሚሉት ላይ ማተኮር እፈጋለሁ። ያኔ አቶ ስዬ መልካም ምክር መክረዉ ነበር። ወያኔ/ኢሕአዴግ ወደ ቀናዉ መንገድ እንዲመጣ፣ ከሕዝብ ጋር እንዲታረቅ ሞክረዋል። ነገር ግን በጎ አስተሳሰባቸዉ ወደ ወህኒ እንዲወረወሩ ተደርገ።

ያኔ አቶ ስዬ ያስተጋቡት የነበረዉን አሁንም በድጋሚ ማስተጋባት እፈልጋለሁ። የገዢዉ ፓርቲ ባለሥልጣናት ልቦናቸዉ ተከፍቶ አሁን እያደረጉት ካለዉ የጭካኔና የከፋት ሄሮድሲያዊ ድርጊት ተቆጥበዉ፣ ወደ ቀናዉ መንገድ እንዲመለሱ እጠይቃለሁ።

ከአቶ ኃይሉ ሻውልና አቶ ልደቱ አያሌዉ ጋር በቤተ መንግስት ዊስኪ መገልበጥ የትም አያደርሳቸዉም። ከሕዝብ ጋር መታረቅ አለባቸዉ። የእልህ ፖለቲካቸዉን ትተዉ በእግዚብሄር ፊትና በህዝብ ፊት እራሳቸዉን ማዋረድ ይኖርባቸዋል። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች የፖለቲካ እሥረኞች በአስቸኳይ መፈታት አለባቸዉ። ጠመንጃ አንስተዋል በተባሉ ወገኖች ላይ የተወሰደዉ አሳፋሪና አስቂኝ የሞት ፍርድ መቀልበስ ብቻ ሳይሆን የታሰሩት ሁሉ ነጻና ገለልተኛ በሆነ ፍርድ ቤት ጉዳያቸዉ እንደገና እንዲታይ መደረግ አለበት።

እነ አቶ መለስ ዜናዊ እንስሳዊ አካሄዳቸዉን አቁሞዉ ጠመንጃ የያዙ ኃይላት ወደ ሰላሙ መንገድ እንዲመጡ ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቻት አለባቸዉ። ከጥላቻና ከጭካኔ የሄሮድስ መንፈስ ወጥተዉ የሰላምና የእርቅ መንፈስን ያስተናግዱ ዘንድ ይገባል።

እንግዲህ ብዙዎቻችን ተናግረናል። ወደፊትም መናገራችንን አናቆምም። የሚሰሙ ከሆነ ይሰሙናል። ካልሰሙንም እንደ ጲላጦስ እጆቻችንን እንታጠባለን። ወደፊት የሚፈጠረዉ መዘዝና ቀዉስ ለራሳቸዉ ብቻ ሳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከነርሱ ጋር ንክኪ ላላቸዉ ሁሉ የሚተርፍ መሆኑን ግን ሊገነዘቡት ይገባል።